በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

***<u>ቦታ፡-</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ጥቅምት ፯ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# <u>የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች</u>

## *መግቢያ*

- ምን ያህሉ ትዳራቸውን ያፈረሱ ወንዶች የተቃጠለ የመብራት አምፑላቸውን በጊዜው ይቀይራሉ? ደንታ አይኖራቸውም፡ ሊያውም ቤት ካላቸው ነው፡፡
- ምን ያህሉ የሥነ ልቦና ምሁራን የተቃጠለ የመብራት አምፑላቸውን በጊዜው ይቀይራሉ? አንድ፡ አምፑሉ ግን ለመቀየር ፈቃደኛ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ሕይወት በርካታ ተስፋ አስቆራጭ አጋጣሚዎች ያሉባት ናት፡፡ ሁሉ ሰው በአንድ ወይ በሌላ ጊዜ እጅ የሰጠ ሆኖ ይሰማዋል፡፡
- እግዚአብሔር ሕይወት ብርቱ ሰልፍ እንደሆነች ስለሚያውቅ በቃሉ በርካታ ማበረታቻዎችን (መጽኛዎችን) ሰጥቶናል፡፡
- ‹‹በምድር ላይ የሰው ሕይወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን?›› <u>*ኢዮ 7፡1፡፡*</u>
- ‹‹መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፡፡›› <u>*ኢዮ 42፡5፡፡*</u>
- የዛሬውም የትምህርታችን ርዕስ ‹‹የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች›› የሚል ነው፡፡

# የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች

## ሀ. እግዚአብሔር ሐሳቡ፣ ዓላማው እና ባሕርይው አይለወጥም

- ‹‹እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ፥ ስለዚህ የጠፋችሁ አይደላችሁም።›› *ሚል 3፡6።*
- ከአንድ ብቻ በቀር ሁሉም ይለወጣል። በርካታ ሰዎች ልክ በየጊዜው ልብሳቸውን እንደሚቀያይሩ ስለ ትዳር ያላቸውን አመለካከት ይለውጣሉ። ዳኞች ወይም ግብር ሰብሳቢ አካላት ውሳኔአቸውን ወይም ሐሳባቸውን ይለውጣሉ፤ ዛሬ ከሥልጣኔው ጋር የሚታየው ‹‹አዲስ የጋብቻ ሥርዓት›› ‹‹ሴት በፈለገችው ጊዜ ሐሳብዋን መለወጥ ስትችል ወንድ ግን የሴቲቱን ይሁንታ ሳያገኝ በፍጹም ሐሳቡን መለወጥ አይችልም።›› የሚል ነው።
- እግዚአብሔር ግን ሐሳቡ ዘወትር አይለወጥም። ትናንትም ሆነ ዛሬ ለዘላለም ያው ነው።
- ሕይወት የማያቋርጥ የጀልባ ጉዞ ስትሆን፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ወደ ወደቡ (ደረቅ መሬት መውጣት ናት። የእግዚአብሔር ቃል ቦታውን እንደሚቀይር ጥላ አይደለም።
- ‹‹አቤቱ፥ ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ይኖራል።›› *መዝ 118(119)፡89*፤ ‹‹እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።›› *ማቴ 5፡18*፣ ‹‹ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።›› *ማር 13፡31።*
- ስለ ወደፊቱ - ከእግዚአብሔርም ጋር ስላለን ነገር የምንለው ሁሉ በማይናወጽ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ጸንተን መቆማችንን ወደ ፊትም በጽኑ እምነት የምንቆም መሆናችንን በማረጋገጥ ነው።

# የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች

## ሰ. እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሁሉ ተቆጣጣሪ ነው

- ‹‹አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኊል፡፡›› *ፊል 4፡19፡፡*
- የሚያስፈልገን ሁሉ ታላቅ ይመስለናል፡ ለቤት፣ ለመኪና፣ ለኢንሹራንስ፣ ለምግብና ለልብስ፣ ለነዳጅ፣ ለሌሎች ጥቃቅን ወጪዎች ብሎም በሺ ለሚቆጠሩ ነገሮች ገንዘብን ወይም ማንኛውንም ነገር እንፈልጋለን፡፡ ዘወትር እንደሚሽከረከር ነገር ግን የትም እንደማይደርስ ወይም እንደማያደርስ ተሽከርካሪ ጎማ ነን… ሁሉ ጊዜ ተመሳሳይ ነገር እንፈልጋለን፡፡
- ነገር ግን የሰው ልጆች ፍላጎት ምንም ያህል የበዛ ቢሆን እግዚአብሔር ግን ሊሞላልን የሚቻለው መሆንኑን ስንረዳ ደስታ ይሰማናል፡፡
- ቀልድ፡- ‹‹ማንኛዋም ሴት በሕይወትዋ አራት ወንዶችን ትፈልጋለች እነርሱም አንደኛው የባንክ ሠራተኛ፣ ሁለተኛው አርቲስት፣ ሦስተኛው ሚኒስትርና አራተኛው የቀብር አስፈጻሚ፡፡ እነርሱንም ለገንዘብ፣ ለመታየት፣ ለዝግጅት፣ እና ለመሸኘት ትጠቀምባቸዋለች››
- እግዚአብሔር የምንሻውን ሁሉ ሳይሆን የምንፈልገውን ይሞላልን ዘንድ የታመነ ነው፡፡ ‹‹ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል፡፡›› *ቀዳ ጢሞ 6፡8፡፡*
- እግዚአብሔር የመበለቲቱ እፍኝ ዱቄትና ጥቂት ዘይት ብቻ መላውን ዓለም መግቦ ለማትረፍ ይበቃዋል፡፡ የሚያስፈልገንን የሚያውቅ አትርፎም ሊሰጠን የታመነ ነውና በቁራ ወይም ከዓሳ ሆድ ውስጥ በተገኘ እስታቴር ሊመግበን ይችላል፡፡ *ማቴ 17፡27፡፡*

# የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች

## ሐ. እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ፈተና ትርጉምና ጥቅም ያሳውቀናል

- ብዙ ጊዜ የሚገጥመን ፈተና የሚፈጽምልን ግዳጅ እንዳለ መገመት ያዳግተናል፡፡ በሂሳብ ደብተራችን ምንም ገንዘብ የሌለን መሆናችን፣ በተለያየ ደዌ መመታታችን ያለምክንያት የሆነ ይመስለናል?
- በዓለሙ ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያዘው የሚያስተዳድረው ሁሉን ቻይ የሆነ እግዚአብሔር በሕይወታችን ያለውን ታናሹን ነገር የማያስተካክለው ይመስለናል?
- ለምንስ ለመከራ አሳልፎ ይሰጠናል? ‹‹የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም፡፡›› *ሮሜ 11፡33*፣ ‹‹የማይመረመረውን ታላላቅ ነገር፥ የማይቈጠረውንም ተአምራት ያደርጋል፡፡›› *ኢዮ 9፡10፡፡*
- አንድ ካህን ወደ አንዲት በነፍስዋ ወደ ተመረረች ሴት ሄዶ ሰላምታ ይሰጣታል፤ ሴቲቱም ሰላምታውን ቸል ብላ የልብስ ስፌት ሥራዋን ቀጠለች፡፡ ሴቲቱም አንድ ሥዕል የሚታይበትን ጥልፍዋን እየጠለፈች እግዚአብሔር ቢሠራ ኖሮ ሕይወቴ እንዲህ መልክ ባላጣ ነበር አለችው፡፡ ካህኑም ስለምን ምንም ትርጉም የሌለው ነገር ትጠልፊያለሽ ብሎ ጠየቃት፤ እርስዋም ያየኸው በሌላ በኩል ስለሆነ እንጂ የምጠልፈው ትርጉም ያለው ጥልፍ

# የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች

## ሐ. እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ፈተና ትርጉምና ጥቅም ያሳውቀናል

- ነው አለችው፡፡ እርሱም የፈለግሁት ይህንኑ ነው፤ አንቺም እግዚአብሔር በሕይወትሽ እየሠራ ያለውን ነገር በተሳሳተ አቅጣጫ ተመልክተሽ እንጂ እርሱ ስለ አንቺ ታላቅ ዓላማ ያለው አምላክ ነው፤ ስለዚህ ከዘለላማዊ ዓላማው አንጻር ጠመልከቺ ብሎ መክሮአታል!!!
- እኛም ከእያንዳንዱ ፈተና ጀርባ ዓላማ እንዳለ ከተገነዘብን መረዳቱ አይከብድም፡፡ ዮሴፍ በባርነት መሸጡ በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ የሌለ ቢሆን መንፈሱን ባጠፋ የእግዚአብሔርንም ዓላማ ባልፈጸመ ነበር፡፡ ስለዚህ ነገሮች የሚመስሉትን መልክ ሳይሆን በፊታችን መልካም የሚያደርገውን እግዚአብሔርን እንመልከት፡፡ ሁሉን በመልካም የሚያስረዳን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፡፡
- ‹‹ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን፤በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም፡፡››***<u>ሮሜ 5፡3-5፡፡</u>***

# የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች

## *መ. ከምንሠራው ኃጢአት የበዛው የእግዚአብሔር ቸርነትና ርኅራኄ*

- በዓለማችን በርካታ አገሮች አንዳንድ ኮርፖሬሽኖች የሚፈልጉትን ለማግኘት በሥልጣን ላይ ያሉትን ይሁንታ (ድጋፍ) መግዛት ያስፈልጋቸዋል፡፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለማግኘት ምንም መግዛት ምንም መክፈል እንደማያስፈልገን ስንረዳ ደስ አይለንም!!!
- ኃጢአታችን ምንም ያህል የበዛች ብትሆን እግዚአብሔር በባሕርይ ልጁ በጌታችን በመድኃኔዓለም ያደረገልን እጅግ ታላቅ ማዳኑን ነው፤ ያለዋጋ ራሱን ስለ ኃጢአታችን አሳልፎ የሰጠንን እግዚአብሔርን እናመስግነው፡፡ ‹‹እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፡፡›› *ቀዳ ዮሐ 3፡16፡፡*

## *ሠ. የእግዚአብሔር ፍቅሩ ፈጽሞ አይተወንም*

- ከባድ ወንጀለኛ ልጅ ያላት እናት ልጅዋን በሕጻንነቱ ወራት በምትወድበት ፍቅር ልክ ትወደዋለች፡፡ እግዚአብሔርም ምንም ብንቃወመው ከመንገዱ ወጥተን የማይረባንንና እርሱንም ደስ የማያሰኘውን ነውር ብናደርግ ፍቅሩ ፈጽሞ እንዲወደን እንጂ ለክፉ አሳልፎ እንዲሰጠን አያደርገውም፡፡ የእግዚአብሔርን ፍቅር ልዩ የሚያደርገውም እንዲሁ እኛን መውደዱን አለማቋረጡ ነው፡፡

# <u>የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች</u>

## *ሠ. የእግዚአብሔር ፍቅሩ ፈጽሞ አይተወንም*

- ከሚታወቁት ሁሉ የሚበልጥ ታላቅ ስበት ያለው እግዚአብሔር ለሰው ባለው ፍቅር ውስጥ ነው፤ ይኸው ፍቅር ሰው እንዲሆን በመስቀል ተሰቅሎ ስለጠላቶቹ እንዲጸልይ አድርጎታል፡፡ *<u>ሉቃ 23፡34</u>*፣ ‹‹ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም፡፡›› *<u>ዮሐ 15፡13፡፡</u>*
- እግዚአብሔርን ብንተወውም ብንርቀውም እንኳ አሁንም እንደሚወደን አውቀን በርትን በንስሐ ወደ እቅፉ እንመለስ፡፡ እኛን ከመውደድ የሚያግደው ምንም ነገር የለምና፡፡
- ‹‹እግዚአብሔርም ከሩቅ ተገለጠልኝ እንዲህም አለኝ፦ በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ፡፡›› *<u>ኤር 31፡3፡፡</u>*

## *ረ. የምትሻለውን ተስፋ እናደርጋለን እንወርሳታለንና*

- የተወለድንበትና ያደግንበት ሥፍራ የተለያየ የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው፣ ደን በበዛበት ተወልደን እጅግ የሠለጠነ ከተማ ውስጥ አድገን ይሆናል፡፡ ወደ ተለያዩ ዓለማትና ቦታዎችም ተጉዘናል፤ ነገር ግን እንደ አባታችን አብርሃም ወደ ዘላለማዊቱ ቤታችን ገና

# የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች

## ፫. የምትሻለውን ተስፋ እናደርጋለን እንወርሳታለንና

- አልደረስንም፡፡ ‹‹አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ስፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፥ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ፡፡ለእንግዶች እንደሚሆን በተስፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖሮ፥ ያን የተስፋ ቃል አብረውት ከሚወርሱ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር፥ እንደ መጻተኛ በእምነት ተቀመጠ፤መሠረት ያላትን፥ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና፡፡›› *ዕብ 11፡8-10፡፡*
- እግዚአብሔር ግን ስለ ዘላለማዊቱ ቤታችን የሚያጽናና ቃሉን ልኮልናል፡፡ ‹‹በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ፡፡በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፥ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ፡፡ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም፡፡ የእግዚአብሔርና የበጉም ዙፋን በእርስዋ ውስጥ ይሆናል፥ ባሪያዎቹም ያመልኩታል፥ ፊቱንም ያያሉ፥ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል፡፡ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፥ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ፡፡›› *ራዕ 22፡1-5፡፡*

# የሚያበረታቱን ሰባት ምክንያቶች

## ሰ. ቅዱሳን ዘወትር ስለሚማልዱልን

- ወላጆቻችን ቅርብ የሆኑ ወዳቾቻችን፣ እህት ወንድሞቻችን ለእኛ ጠቃሚ በሆነ ጉዳይ ጥያቄ አቅርበውልን ተቀባይነት እንደሚያገኙ ሁሉ የዚህን ዓለም ውጊያና ፈተና በድል ተወጥተው የፈጸሙትና እግዚአብሔር የወሰዳቸው ቅዱሳን እንዲሁም ቅዱሳን መላእክት ስለኛ ዘወትር ይማልዱልናል፡፡ ‹‹መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ›› ***ማቴ 18፡10***፣ ‹‹የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ ታላቅ ኃይል ታደርጋለችና፡፡›› ***ያዕ 5፡16፡፡***
- ይህም ምልጃቸው በእኛና በቅዱሳኑ መካከል ያለውን ከእግዚአብሔር የሆነውን ፍቅር ያሳየናል፡፡ ጸሎታቸውም ከንጹሕ ዕጣን ጋር ወደ እግዚአብሔር ደርሳ የተትረፈረፈ በረከትና መገብኘት ከእግዚአብሔር ለእኛ እንድትደርስ ትሆናለችና እንበርታ እንጂ አንታወክ፡፡ ‹‹የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ፡፡›› ***ራእ 8፡3-4፡፡***
- እመቤታችንም የምታቀርብልን ልመና እናት ለልጆችዋ የምታቀርበው ልመና ነው፡፡
- ዛሬ ላይ ለደረስንበት ማዕረግ ከእኛ ያልተጠየቀ ነገር ግን ከወላጅ እናታችን ከእንባ ጋር የተቀላቀለ ስኬታችንን፣ ጤናችንን፣ … የሚጠይቅ ልመና ወደ መንበረ ጸባዖት አልቀረበልንም ይሆን? እንዲሁ የሚማልዱልን እንደ ከዋክብት የሆኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኘናቸው ቅዱሳን በዙሪያችን አሉልንና እንበርታ እንጂ አንስነፍ!!! ***ዕብ 12፡1፡፡***

ስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር፡፡ አሜን!!!

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org